

# ኢየሱስን አካፍሉት

ትምህርት 12 ለ ሰኔ 13፣ 2018



“የደከመውን በቃል
እንዴት እንደምደግፍ
አውቅ ዘንድ ጌታ
እግዚአብሔር የተማሩትን
ምላስ ሰጥቶኛል፤ ማለዳ
ማለዳ ያነቃኛል፥ እንደ
ተማሪዎችም ትሰማ ዘንድ
ጆሮዬን ያነቃቃል።”
(ኢሳይያስ 50:4)

ብዙ ሺሆች ኢየሱስን የእውነት አያውቁትም። እኛ "የጠፉ በጎች" ብለን እንጠራቸዋለን ነገር ግን እነርሱ መጥፋታቸውን እንኳን አያውቁም። ታዲያ ኢየሱስ እንደሚያስፈልጋቸው አንድ ሰው ካልነገራቸው እንዴት ያውቃሉ?

እግዚአብሔር በምድር ላይ ላሉ ሰዎች በሙሉ ስለሚገድደው "ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ" ይወድዳል (1 ጢሞ 2:4)። ይህ ደግሞ እርሱን የማያውቁትንና አውቀውትም ደግሞ ከመንገዱ የተመለሱትን ሰዎች ሁሉ ያጠቃልላል።



እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ ሰዎች ለመድረስ የመረጠው መንገድ ምንድን ነው? በእኛ በኩል ነው። ይህ የእኛ "ታላቁ ተልዕኮአችን" ነው።





## ስለ ምን እናካፍል?

- ታላቁ ተልዕኮ

## እንዴት ልናካፍል እንችላለን?

- የኢየሱስን መንገድ መከተል
- ወዳጅነትን ማጠናከር

## ያፈገፈጉትን እንዴት መመለስ ይቻላል?

- እግዚአብሔር ልጆቹን እየፈለገ ነው
- የጠፋውን እየፈለግን እንገኛለን

# ስለ ምን እናካፍል?

# ታላቁ ተልዕኮ


"ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ሥም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው" (ማቴዎስ 28:19)



"ወደ አሕዛብ [ሁሉ] …ሂዱ" ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ሊያዩት ለተሰበሰቡት ሰዎች የሰጠው ትዕዛዝ ነው (ማቴ 28:18-19)።




የተሰጣቸው ተግባር ምንድን ነበር? ሊሄዱና አሕዛብን ደቀ መዛሙርት ሊያደርጉ ነበር። ይህም ማለት ሰዎችን ሊገናኙ፣ ሊያጠምቋቸው እና የኢየሱስ ተከታዮች እንዲሆኑ ሊያስተምሯቸው ነበር (ማቴ 28:19-20)።



እነዚያ ደቀ መዛሙርት ደግሞ በተራቸው ሌሎች ደቀ መዛሙርትን ያፈራሉ… እናም እንዲህ እያለ ለሁለት ሺህ ዓመታት ከቆየ በኋላ … የእኛ ዘመን ላይ ደርሷል። አሁን ይህን የኢየሱስ ትዕዛዝ የምንቀበለው እኛ ነን።

እንደ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ "እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም" (የሐዋ 4:20)። ከመድረክ ላይ ሆነን ልንሰብክ እንችላለን፣ በመንገድም ላይ ልንጮህ እንችላለን፣ ምስክርነታችንን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ወይም ደግሞ ለአንድ ሰው ልንነግር እንችላለን። ሁላችንም በዚህ እንሳተፋለን።



# እንዴት ልናካፍል እንችላለን?

# የኢየሱስን መንገድ መከተል

“የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ ምክንያቱም አንዱ ስለ ሁሉ እንደ ሞተ እርግጠኞች ሆነናል፣”
(2 ቆሮንቶስ 5:14 አ.መ.ት)

ኢየሱስ “የጠፋውን በግ” እንዲፈልግ ያነሳሳው ምንድን ነበር (ማቴ 15:24)?

ለእኛ ያለው ፍቅር እንደሆነ የማያጠራጥር ነው (ማቴ 9:36፣ ኤፌ 5:2)። ደግሞም ኢየሱስን ላላወቁት እናካፍላቸው ዘንድ ፍቅሩን በውስጣችን አስቀምጦልናል። አንዳንድ ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሌሎች ኢየሱስን እንዲቀበሉ ያስገድዳሉ። እግዚአብሔር ግን የመረጠው መንገድ እንዲህ አይደለም።








እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ኃጥያት እንዳይሰሩ አላስገደዳቸውም። በኖኅ ዘመንም ሕዝቡን ወደ መርከቢቱ እንዲገቡ አላስገደዳቸውም። የነነዌን ሰዎች እንዲቀበሉት አላስገደዳቸውም ነበር። በፍቅር ተናገራቸውና ከክፉ መንገዳቸው ካልተመለሱ ስለሚከተሉት ውጤቶች አስጠነቀቃቸው ።

የኢየሱስን አርአያ በመከተል ፍቅሩን ለሌሎች በማሳየት እርሱን እንዲከተሉ መጋበዝ አለብን።

# ወዳጅነትን ማጠናከር

"…ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።."
(1 ጴጥሮስ 3:15)

እኛ ሁላችንም የኢየሱስ ሰባኪዎች ስንሆን ለዚህም ተግባር ዝግጁዎች እንድንሆን ታዘናል (1 ጴጥ 3:15)። ነገር ግን ሁላችንም የመስበክ ችሎታ የለንም። የሚያስፈልጉንን ቃላቶች ደግሞ እግዚአብሔር እራሱ እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል (ኢሳ 50:4)።




ኢየሱስን ለሌሎች ስናካፍል የበለጠ የታሰበበት እንዲሆን የሚያግዙ ቀላል ምክሮችን እስኪ እንመልከት፡


አንድን ሰው መተዋወቅና በጊዜ ሂደት ወዳችነትን መገንባት


በዚያ ሰው ልብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንዲሰራ መጸለይ፤ ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር ትክክለኛ ጊዜን ለማግኘት መጸለይ


ስለ ግል የእምነት ልምምዳችሁ የምትናገሩበት ቀላል መንገድ ፈልጉ ወይም ለሰዎቹ ፀልዩላቸው


አዲስ ወዳጃችሁን በቤተክርስቲያናችሁ ካሉ ከሌሎች ጋር ለማገናኘት መንገዶችን ፈልጉ


ይህ ወዳጃችሁ ግራ የገባው ነገር ካለ ወይም የሚያስፈልገው ነገር ካለ ፀልዩለት


መጽሐፍ ቅዱስ ለህይወታችን መጽናናትን፣ ምክርንና ምሪትን እንዴት እንደሚሰጥ ለማሳየት መንገዶችን ፈልጉ


ወዳጃችሁን መጽሐፍ ቅዱስ አብሮአችሁ የማጥናት ፍላጎት እንዳለው የምትጠይቁበት ጊዜ ደግሞ ይመጣል። ከቆይታ በኋላ ምናልባት መጠመቅን ሊፈልጉ ይችላሉ።


# ያፈገፈጉትን እንዴት መመለስ ይቻላል?

# እግዚአብሔር ልጆቹን እየፈለገ ነው

“በእውነት ኤፍሬም ለእኔ የከበረ ልጅ ነውን? ወይስ የተወደደ ሕፃን ነውን? በእርሱ ላይ በተናገርሁ ቍጥር አስበዋለሁ፤ ስለዚህ አንጀቴ ታወከችለት ርኅራኄም እራራለታለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር” (ኤርምያስ 31:20)



በአንድ ወቅት ላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተከፋፈሉ: ኤፍሬም (የሰሜኑ መንግስት) እግዚአብሔርን ካደ፤ ይሁዳ (የደቡቡ መንግስት) ደግሞ ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበሩ።



እግዚአብሔር ኤፍሬም ቢክደውም አሁንም ውድ ልጄ እያለ ይጠራው ነበር (ኤር 31:20)። አያቱ ራሄልን እንኳን በኃጥያታቸው ለሞቱት ልጆቿ እንደምታለቅስ አድርጎ ይናገራል (ኤር 31:15)።

እግዚአብሔር አገልግለውት ከዚያ የካዱትን ሰዎች በፍቅር መጥራቱን አላቋረጠም። አሁንም ልጆቹ ናቸው፤ ይወዳቸዋል እና ወደ እርሱም እንዲመለሱ ያለማቋረጥ ይጠራቸዋል።



ምናልባት ከራሳችን ልጆች አንዳንዶቹ ቀድመው እምነትን የያዙ አሁን ግን የተዉት ይኖራሉ። ጀርባችንን እነርሱ ላይ ከማዞር ይልቅ እነርሱን መውደድና በፍቅር ማናገር መቀጠል አለብን። እግዚአብሔር የጥልቅ ርኅራኄው ማረፊያ እንደሆኑና ወደ እርሱ እንዲመለሱ ከልቡ እንደሚፈልግ ያስታውሰናል።

# የጠፉውን እየፈለግን እንገኛለን

"በአሕዛብም መካከል ብዘራቸው እንኳ በሩቅ አገር ሳሉ ያስቡኛል፥ ከልጆቻቸውም ጋር በሕይወት ይኖራሉ፥ ይመለሱማል።"
(ዘካርያስ 10:9)





ባለቤታችን፣ ወንድ ልጆቻችን፣ ሴት ልጆቻችን፣ ጓደኞችን፣ ጎረቤታችን፣ በቤተክርስቲያን ጊባኤ ውስጥ አብሮን ሲቀመጡ የነበሩ ወንድምና እህቶቻችን ... በአንድ ወቅት አብረውን ሲያመልኩ ነበር፤ አሁን ግን የት አሉ?

ሰዎች ከቤተክርስቲያን የሚርቁበት ብዙ ምክንያት አለ። ምክንያቶቻቸውን ልንተች ወይም ደግሞ ልንረሳቸው አይገባም።

የእኛ ሚና ካሉበት ሄደን እነርሱን ወደ መንጋው መመለስ ነው። ይህን የምናደርገው እንዴት ነው? በመጀመሪያ መጸለይ። ሁለተኛ ደግሞ ለእነርሱ የፍቅርና የመልካምነት ተምሳሌት በመሆን ነው።

የእናንተ የህይወት ምስክርነት፣ ድርጊታችሁ፣ ንግግራችሁ እና ጸሎታችሁ ከእግዚአብሔር ለራቁ ሰዎች ህይወታቸውንና የወደፊት እጣፈንታቸውን መቀየር ይችላል።



“እግዚአብሔር የወንጌልን መልዕክትና የፍቅርን አገልግሎት በሙሉ ለሰማያዊ መላዕክት ማስረከብ ይችል ነበር። ዓላማውን ለማሳካት ሌሎች መንገዶችን መምረጥ ይችል ነበር። ነገር ግን ከማያልቀው ፍቅሩ የተነሳ ከእርሱ፣ ከክርስቶስ እና ከመላዕክቱ ጋራ እንድንተባበርና ከዚህ በጎ ተግባር በሚገኘው በረከት፣ ደስታ እና መንፈሳዊ ከፍታ ተካፋዮች እንድንሆን እኛን። [...]

ክርስቶስ እንደሚፈልገው ወደ ስራው ከሄድንና ነፍሳትን ለእርሱ ከማረክን ሰማያዊ ነገሮችን የማወቅና በጥልቅ የመለማመድ አስፈላጊነት እንረዳለን፤ ከዚያም ጽድቅን መራብና መጠማት እንችላለን። እግዚአብሔርን ስትማፀኑት እምነታችሁ ይጠነክራል፤ ነፍሳችሁም ከመዳን ጉድጓድ በጥልቀት ትጎነጫለች። ተቃርሮና ፈተና ወደ መጽሐፍ ቅዱስና ወደ ጸሎት ይመሩናል። በጸጋ ደግሞም ክርስቶስን በማወቅ ታድጋላችሁ እናም የበለጸገ ልምምድን ታገኛላችሁ”።

EGW (The Way to Christ, pp. 79-80)